# የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ ላይ የተዘጋጀ ማብራርያ

## መግቢያ

በአንድ ሀገር ዉስጥ በሚደረግ የፍትህ አስተዳደር ስራ ዉስጥ ጠበቆች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማተፍ ፍትህ እና የህግ የበላይነት ተከብሮ የሚኖርባት ሀገር እዉን በሚደረግ ሂደት ከፍተኛ ሚና የሚጫዉቱ አካላት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ይኸዉም የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብት እና የህግ የበላይነት የሚረጋገጥበት አንደኛዉ መንገድ ፍትህን የሚሹ ዜጎች በጠበቆች ወይም ጥብቅና ድርጅቶች ተገቢዉን የህግ ምክር ሲያገኙ እና በአግባቡ ሲወከሉ ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን የህግ የበላይነት እና የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብትን በሚረጋገጥ ሂደት ጠበቆች የሚጠበቅባቸዉን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል በፌደራል ደረጃ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992፤ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/1992 እና የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 65/1992 እንዲሁም በክልሎችም ተመሳሳይ ህጎች ወጥተዉ እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡

ይሁንና በእነዚህ ህጎች መሰረት በሚሰጠዉ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ላይ ሰፋ ያለ የህግ እና የአሰራር፤ እንዲሁም ከጠበቆች ብቃት እና ሥነ ምግባር ጋር የተያያዙ ችግሮች እየተስተዋሉ መሆኑን በተቋማችን በተደረገዉ ሀገር አቀፍ ጥናት ለማወቅ እና ለማየት ተችሏል፡፡ ከተለዩትም ችግሮች መካከል ነጻ የጥብቅና አገልግሎት በአግባቡ ማካካት የሚስችል ማለኪያ አለመቀመጡ፣ ባልታደሰ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ጠበቆች መቆጣጠር የሚቻልበት አሰራር አለመቀመጡ፤ ፍቃድ አለማደስ በቀጥታ የዲሲፕሊን ጥፋት ከመደረጉ በፊት ሌሎች አማራጮች አለመቀመጣቸዉ፤ የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ ገለልተኛ አለመሆን እና ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የዉሳኔ ሀሳብ ከማቅረብ ባለፈ በራሱ ዉሳኔ የሚሰጥ መሆኑ፤ በዲሲፕሊን ጉዳይ ይርጋ፤ ደጋጋሚነት እና ማስየምን የመሳሰሉ ሀሳቦች ያልተካተቱ መሆኑ፤ በህግ መሰረት ጉዳይ አጥርተዉ በሚይዙ ፤ ተገቢዉን ክርክር በሚያደርጉ፣ ምስክር እና ተከሳሽ በሚያስጠኑ፣ ደንበኛ እና ተከራካሪ ወገንን ባከበረ መልኩ ክርክር በሚያደረጉ እና ሌሎች የስነ-ምግባር ጉድለት ባለባቸዉ ጠበቆች ላይ ተገቢዉን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ተመጣጣኝ የዲሲፕሊን ቅጣት እንዲቀጡ አለማድረግ ዋና ዋናዎቹ በጥብቅና አገልግሎቱ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ናቸዉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሚሰጠዉ የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በመንግስት (ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ) ቁጥጥር ስር መሆኑ አገልግሎቱ በሚጠበቅበት ደረጃ እንዳያድግ እና የሙያ ነጻነቱን በአግባቡ በጠበቀ መልኩ እንዳይሄድ ክፍተት ያለ በመሆኑ፤ እንዲሁም በስራ ላይ ያሉት የጥብቅና ህጎች ሀገሪቱ ካለችበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች አንጻር ሊኖሯት የሚያስፈልጉ የጥብቅና ድርጅቶችን በተደራጀ ሁኔታ የሚገዙ አለመሆናቸዉ፤ እንዲሁም ከጠበቆች ዲሲፕሊን ክስ እና ቅጣት አንጻር ይርጋ፣ ደጋጋሚነት፣ ማስየም የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚዳስሱ አለመሆናቸዉ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

በማሁኑም እነዚህን እና ሌሎች በጥናት ሰነዱ የተለዩ ችግሮችን ለፈታ የሚችል፣ የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ስርዐቱን ወጤታማ በሚድረግ የጠበቆችን መብት እና ነጻነት ባስጠበቀ ሚሉኩ የተገልጋዮችን መብት ለማስከበር እና ብሎም ጠበቆች ትክክለኛ የፍትህ ባለድርሻ አካል ሆነዉ እንዲሰሩ ለማስቻል እና በሌሎች በረቂቅ አዋጁ መግቢያ ላይ በተጠቀሱ ምክያቶች ይህንን አዋጅ ሚርቀቅ አስፈልጓል፡፡

## 1. ረቂቅ አዋጁ በሚዘጋጅበት ጊዜ የነበረው ሂደት

የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን የሚርቀቅ ስራ በቅድሚያ የተከናወነዉ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስር በተቋቋመዉ የህግ እና ፍትህ ማሻሻያ ጉባኤ ሲሆን ይህ አካል ያረቀቀዉ ረቂቅ በማስረቱ ጥሩ ጥሩ የሆኑ አዳዲስ ሀሳቦች የተካተቱበት ቢሆንም አብዛኛዉ የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ስራን ገና አዲስ ለሚቋቋመዉ የጠበቆች ማህበር የሚሰጥ በማሆኑ፤ እንዲሁም የማህበሩን አቅም ሚጎርጀት እና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመቆጣጠር የማችልበት ሁኔታን መፍጠር ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ በማሆኑ በዚህ ማሀል ባለሚዉ እና ደንበኞች ላይ ጉዳት ሊደርስ ስለሚችል በሚል እሳቤ በጉባኤዉ የተዘጋጀዉ ረቂቅ ቀሪ ተደርጎ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ህግ ጥናት፣ሚርቀቅ እና ማስረጽ ዳይሬክቶሬት ይህ ረቂቅ እንደ አዲስ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረቂቅ አዋጅ የመጀመሪያ ረቂቅ ላይም የጉባኤዉ አባላት እና ሁሉም የፌደራል ጠበቆች የተገኙበት መድረክ በማዘጋጀት ግብአት በማሰብሰብ ማስተካከያ በሚድረግ ረቂቁ አሁን ባለዉ ሚልክ ተዘጋጅቷል፡፡ ረቂቁ ሲዘጋጅም በጉባኤው ስር የተቋቋመው የስራ ቡድን ያጠናወን ጥናትና ያረቀቀወን ረቂቅ እንዲሁም በህግ ጥናት ሚርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት በጥብቅና ስርአቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች በሚል ርእስ የተጠናወን ጥናትና የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮ በመወሰድ ነው፡፡

## 2. የረቂቅ አዋጁ ዝርዝር ይዘት

### 2.1. ክፍል አንድ

የአዋጁ ክፍል አንድ (ከአንቀጽ1-3) ስለ ጠቅላላ ድንጋጌዎች የሚዎትት ሆኖ የአዋጁን አጭር ርዕስ፣ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት እና ሀረጎችን ትርጓሜ እና የተፈጻሚነት ወሰንን አካቷል፡፡ ተፈጻሚነት ወሰንን በተማለከተ ይህ አዋጅ በዚህ አዋጅ ማሰረት ማሟላት የሚጠበቅባቸዉን ማስፈርቶች አሟልተዉ የጥብቅና ፍቃድ በተሰጣቸዉ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ላይ እንዲሁም በሀገር ወስጥ በሚሰሩ የዉጭ ሀገር ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ይኸዉም ይህ አዋጅ የፌደራል ፍርድ ቤት ፍቃድ ብቻ ከሚያወጡ /ካወጠ/ በተጨማሪ የክልል ጥብቅና ፍቃድ ይዘዉ በዚህ አዋጅ ማሰረት የጥብቅና ፍቃድ በሚያወጠ/አዉጥተዉ እየሰሩ ባሉ ጠበቆች እና ወደፊት በሚቋቋሙ የጥብቅና ድርጅቶች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በረቂቁ አንቀጽ 8 ማሰረት

ወደ ሀገር ዉስጥ ገብተዉ በሚሰሩ የዉጭ ሀገር ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች አዋጁ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተቀምጧል፡፡

## 2.2. ክፍል ሁለት

የአዋጁ ክፍል ሁለት(ከአንቀጽ 4-21) ስለ ፍቃድ አሰጣጥ፤ ምዝገባ እና እድሳት የሚያትት ሲሆን በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ማለትም ንዑስ ክፍል አንድ(ከአንቀጽ 4-16) ስለ ፍቃድ አሰጣጥ እንዲሁም ንኡስ ክፍል ሁለት(ከአንቀጽ 17-21) ስለ ፍቃድ ምዝገባ እና እድሳት ያትታሉ፡፡ በንዑስ ክፍል አንድ ስር አጠቃላይ ከጥብቅና ፍቃድ ጋር በተያያዘ ሊከተል ስለሚገቡ መርሆዎች የሚዘረዝር ሲሆን የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ ሊኖረዉ እንደሚገባ፤ ይህን ፍቃድ ለማዉጣት ደግሞ በቋሚ ስራ ላይ የተሰማራ መሆን እንደሌለበት፤ እና ሌሎች በዚህ አዋጅ የተቀመጡት ማስፈርቶችን አሟልቶ ማግኘት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ይሁንና ለራሱ ጉዳይ የሚከራከር፤ ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛው፣ ለወላጁ፣ ለልጁ፣ለአያቱ፣ለእህቱ፣ለወንድሙ፣ለትዳር ጓደኛዉ ወላጆች፣ ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰዉ የሚከራከር፣ ከስራዉ ጋር በተያያዘ የሚከራከር ዐቃቤ ህግ፤ ህጋዊ ሰዉነት ባለዉ የንግድ ድርጅት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፤ ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማህበር፣ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም በሌላ አግባብነት ባለዉ ህግ ማስረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፤ የመንግስት ማስርያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚወክለት የሚከራከር ማንኛዉም የመንግስት ማስርያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሀላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰው፤ ወይም ማንኛዉም የሰራተኛ ማህበር ሜ ወይም ማህበሩ የሚወክለዉ ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልግ የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት የሚችል መሆኑ ተቀምጧል፡፡

ነገር ግን ከላይ ከተዘረዘሩት አካላት ዉጪ ያለ ማንኛዉም ሰዉ የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት የሚያስችለዉን ፍቃድ ለማግኘት ፍቃድ ጠያቂዉ አንደኛ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለዉ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ መሆን እንዳለበት (ምክንያቱም የህግ አገልግሎት የዉጪ ዜጎች ማስማራት የማይችሉበት አገልግሎት በመሆኑ)፤ ሁለተኛ የስራ ሚለቀቂያ እና የስነምግባር ሁኔታ ለማወቅ ስራዉን ከሚለቀቁ በፊት ይሰራበት በነበረዉ ተቋም ዉስጥ ባለዉ ሁለት አመት ዉስጥ በከባድ ዲሲፕሊን ያልተቀጣ መሆኑን የሚገልጽ ሚረጋገጫ ማቅረብ እንዳለበት፤ ሶስተኛ በህግ ሙያ የስራ ልምድ ያለዉ እና የሙያ መግቢያ ፈተና ያለፈ፤ እና ዕዉቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ መሆን እንዳለበት ጠቅላላ ማስፈርቶች የተቀመጡ ሲሆን ለየጥብቅና ፍቃድ አይነቱ የሚያስፈልገዉ ዝርዝር ማስፈርቶችም በረቂቁ ከአንቀጽ 12-14 ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ ከትምህርት ጋር ተያይዞ በዉጭ ሀገር በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ላላቸዉ ሰዎች ማእቀፍ ማበጀት ስለሚያስፈልግ ከኢትዮጵያ ዉጪ ካለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ በአንቀጽ 12(2)፤ 13(2) እና 14(2) ማስረት እንደየ

ጥብቅና ፍቃድ አይነቱ የሚጠየቀዉ የስራ ልምድ በኢትዮጵያ ዉስጥ ዲግሪዉን ካገኘ ሰዉ ከፍ ያለ ቢሆንም ሌሎች ማስፈርቶችን እስካሟላ ድረስ የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጥብቅና ፍቃድ በአንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሱትን ለሟሟላት፤ ታስቦ በሚፈጸም እና ከሙያ ስነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ ሶስት አመት እና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ለተባለ እና አግባብነት ባለዉ ህግ ላልተሰየመ ወይም ደግሞ በህግ አገልግሎት እንዳይሰማራ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ክልከላ ለተጣለበት አንደማይሰጥ በግልጽ ተመላክቷል፡፡ ሌላዉ በዚህ ረቂቅ አዋጅ እንደ አዲስ የተካተተዉ የዉጭ ሀገር ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶችን በሀገር ዉስጥ በወሰን ጉዳዮች እና ሁኔታ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደ ሲሆን ይኸዉም የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥበት ጉዳይ ጠበቃዉ ወይም ጥብቅና ድርጅቱ ፍቃድ ያገኘበትን ሀገር ህግ የሚመለከት ሲሆን እና ፍቃድ ካገኘ የአገር ዉስጥ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ጋር በመሆን ነዉ፡፡ የዉጭ ሀገር ጠበቆችን እና ጥብቅና ድርጅቶች በሀገር ዉስጥ እንዲሰሩ መፍቀድ ያስፈለገበት የዕዉቀት ሽግግር እንዲኖር እና ሀገሪቱ ለምታደርጋቸዉ ዓለም አቀፍ የህግ ክርክሮች ለዉጭ ሀገር የህግ ባለሙያዎች የምታወጣዉን ከፍተኛ ክፍያ በማስቀረት በሂደት በዚህ እዉቀት ሽግግር በዳበሩ የሀገር ዉስጥ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች እንድትወከል በማስቻል ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ ይቻላል ከሚል እሳቤ ነዉ፡፡

ሌላዉ የፍቃድ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ አሁን ባለዉ አሰራር የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጠዉ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ነዉ፡፡ ይህ አሰራር ወይም አንድ ሰዉ በጥብቅና ሙያ ላይ የመሰማራት ትልቅ መብቱን በመንግስት አካል እንዲወሰን ሲደረግ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ነጻ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ማሰጠቱ ላይ ጥያቄ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ የጥብቅና ሙያ በሂደት ነጻ እና ራሱን የሚያስተዳድርበትን መንገድ የሚዘጋ በመሆኑ በዚህ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 9(1) የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰጥ የመወሰን ስልጣን ለጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ የተሰጠ ሲሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ደግሞ የጸሀፊነት ሚና ኖሮት በኮሚቴዉ ለተወሰነለት ሰዉ ፍቃድ እንዲሰጥ በማድረግ የፍቃድ አሰጣጡን ገለልተኛ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

በዚሁ አግባብ በአንቀጽ 9(2)-(4) በተደነገገዉ የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ፍቃድ እንዲሰጥ ወይም አንዳይሰጥ ዉሳኔ የሚሰጥባቸዉ የግዜ ገደቦች ተለያይተዉ ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህን ቀነ ገደቦች ለያይቶ ማስቀመጥ ያስፈለገዉ ግልጽነት ያለዉ አሰራር እንዲኖር ለማስቻል እና አመልካቾች ላይ የሚደረግ አላግባብ እንግልት ለማስቀረት ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አሁን ባለዉ አሰራር ከፍቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በቀጥታ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ይል የነበረ ሲሆን በዚህ ረቂቅ አዋጅ ግን በፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ጉዳዩን ይዞ ወደ ፍርድ ቤት ከማምራቱ በፊት በአስተዳደራዊ መንገድ የሚፈታበትን ሁኔታ አሟጦ ለመጠቀም በማሰብ ጉዳዩን በቅድሚያ ገለልተኛ

አካል ወደሆነዉ የጠበቆች ቦርድ እንዲታይ በይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል፤ ከዚህም በመቀጠል የቦርዱ ዉሳኔ በታወቀበት 30 ቀናት ዉስጥ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድበትን ሁኔታ ተቀምጧል፡፡

የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶችን በተመለከተ በስራ ላይ ካለዉ አዋጅ በተመሳሳይ ሜሉኩ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፤ የፌደራል ማፕቸዉም ፍርድ ቤት እና የፌደራል ልዩ የጥብቅና ፍቃድ ተብለዉ የተከፈሉ ሲሆን የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸዉ ማስፈርቶች አብዛኛዉ በአንቀጽ 6(1) ስር ከተዘረዘሩ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ አሁን በስራ ላይ ባለዉ አዋጅ በህግ ሙያ ሁለት አመት ልምድ ይጠይቅ የነበረዉ ወደ ሶስት አመት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ይህም የሆነበት አሁን በረቂቅ ላይ ባለዉ የወንጀል ስነስርዓት ህግ እና እየተሻሻለ ባለዉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሚደራጃ አዋጅ ማስረት አብዛኛዉ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይታዩ የነበሩ ጉዳዮች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ታሳቦ እየተሰራ በመሆኑ በእነዚህ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ጉዳዮችን የሚይዙ ጠበቆች የተሻለ የስራ ልምድ ሊኖራቸዉ ይገባል ከሚል እሳቤ ነዉ፡፡ ሌላዉ ምንም እንኳን በአሁን ጊዜ በህግ በዲፕሎማ ፕሮግራም ማስተማር የቆመ ቢሆንም ካሁን በፊት በዲፕሎማ ተመርቀዉ በተለያዩ ማስርያ ቤቶች በህግ ባለሙያነት እያገለገሉ ያሉ ባለሙያዎች በመኖራቸዉ እነዚህ ሰዎች የሚቀርቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የጥብቅና ፍቃድ ጥያቄ ምላሽ ማስጠት ስለሚያስፈልግ በነባሩ ህግ የተቀመጠዉ ዲፕሎማ እና አምስት አመት የስራ ልምድ በዚህ ረቂቅም እንዲካተት ሆኗል፡፡ እንዲሁም በዉጭ ሀገር የሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ ሰዉን በተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍቃድ ለማግኘት በህግ ሙያ አምስት አመት ልምድ እና ሌሎች ለደረጃዉ የተቀመጡ ማስፈርቶችን ማሟላት እንዳለበት ተቀምጧል፡፡

የፌደራል ማፕቸዉም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድን በተመለከተም አብዛኛዉ ማስፈርቶች ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍቃድ ማስፈርቶች ጋር ተመሳሳይ ሆነዉ በተለየ ሜሉኩ የተቀመጠዉ በህግ ሙያ ቢያንስ የአምስት አመት ልምድ ሊኖር እንደሚገባ ማለጹ ነዉ፡፡ የዉጭ ሀገር ዲግሪ ያላቸዉን በተመለከተም ሌሎች ማስፈርቶችን ማሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ሙያ ለሰባት አመት ማገልገል እንደሚኖርበት ተጠቅሷል፡፡ የዉጭ ሀገር ዲግሪ ላላቸዉ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ለማፕቸዉም ፍርድ ቤት ፍቃድ ለማዉጣት ከሌሎች ይልቅ የስራ ልምዱን ከፍ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት በዉጭ ሀገር የተማሩ የሀገሪቱን ህጎችን በተመለከተ እዉቀት እና የስራ ልምድ ለማካበት በሀገር ዉስጥ ከተማሩት ሰዎች ይልቅ ተጨማሪ ግዜ ሊወስድባቸዉ ይችላል በሚል እሳቤ ነዉ፡፡ እንዲሁም ልዩ የጥብቅና ፍቃድን በሚመለከት ይህ ፍቃድ ሰዎች ወይም አካላት አሁን በስራ ላይ ባለዉ አዋጅ ከተጠቀሱት ድርጅቶች በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ህግ ትምህርት ቤቶች እና ማምህራን እንዲያገኙ ተደንግጓል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ አካላት የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት የሚያስችል አቅም እያላቸዉ በአካባቢያቸዉ ላሉ አቅም ለሌላቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የህግ ድጋፍ ለማስጠት ፍላጎት ቢኖራቸዉም የጥብቅና ፍቃድ የሚያገኙበት አግባብ ያልነበረ በመሆኑ ይህን ታሳቢ በማድረግ ልዩ የጥብቅና ፍቃድ እንዲገኙ ተደርጓል፡፡

ሌላዉ በዚህ ረቂቅ አዋጅ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያስተምሩ የህግ መምህራን የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጥበት አግባብን በተመለከተ ለረጅም ግዜ ጥያቄ ሲነሳበት እና ሲያከራክር የነበረ ሲሆን ይህን ለመፍታት እነዚህ መምህራን የጥብቅና ፍቃድ ቢሰጣቸዉ የንድፈ ሀሳብ እና ተግባራዊ የህግ እዉቀት እና ክህሎት በማዳበር ተሞክሮዎቻቸዉንም በዚሁ አግባብ የመቅረጽ ሁኔታን ያመቻቻል እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ የማስተማር ስራቸዉን እየለቀቁ ያሉ መምህራኖችን በማስቀረት በተረጋጋ ሁኔታ የመማር ማስተማር ስራቸዉን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ያስችላል የሚል እሳቤ በመያዝ በዚህ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 15(1) ላይ እንደተገለጸዉ ኢትዮጵያዊ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የህግ መምህራን ብቻ ስራቸዉን መልቀቅ ሳያስፈልጋቸዉ የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጣቸዉ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በጥብቅና ላይ ሲሰማሩም የመማር ማስተማር ስራዉን እንዳይጎዱ በማሰብ በአንቀጽ 15(2) ላይ የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰጠዉ የሚጠይቅ መምህር የጥብቅና ስራዉ የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዳለበት ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱም እነዚህን መምህራን የሚቆጣጠሩበት አሰራር ማዘርጋት ሊጠበቅባቸዉ ይችላል፡፡

የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተናን በተመለከተ ማንኛዉም በጥብቅና ሙያ ላይ ማሰማራት የሚፈልግ ሰዉ በመርህ ደረጃ የመግቢያ ፈተና መዉሰድ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን 5 አመት በፌደራል ፍርድ ቤቶች ላገለገሉ ዳኞች ወይም ዐቃቤ ህጎች፣ በማንግስት ማስርያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት በህግ አማካሪነት/ ባለሙያነት ወይም ነገረ ፈጅነት ያገለገለ፤በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለ7አመት የህግ መምህር ሆኖ የሰራ ኢትዮጵያዊ በልዩ ሁኔታ ያለፈተና የጥብቅና ፍቃድ እንዲያገኙ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪም በማንግስት ማስርያ ቤት ወይም ልማት ድርጅት ከሚሰሩ የህግ አማካሪ ወይም ባለሙያ ወይም ነገረፈጅ ጋር ተመሳሳይ አንዳንዴም የተሻለ የስራ ልምድ ያላቸዉ በረዳት ዳኝነት፣ በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት የህግ ጉዳይ ፀሐፊነት ወይም የጠበቃ ረዳትነት፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ በሀይማኖት ተቋማት፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በንግድ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት በህግ አማካሪነት ወይም በህግ ባለሙያነት ወይም በነገረፈጅነት የሚያገለግሉ ሰዎችም የሰባት ዓመት ልምድ ያላቸዉ እንደሆነ ያለፈተና ፍቃድ እንደሚሰጣቸዉ ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍቃድ ያላቸዉ ጠበቆች ወደ ማዕከላዊ ፍርድ ቤት ፍቃድ ማሳደግ የሚፈልጉ ከሆነ ቀድሞ በያዙት ፍቃድ አምስት አመት የሰሩ እና በህግ ዲግሪ ካላቸዉ ያለፈተና የማዕከላዊ ፍርድ ቤት ፍቃድ ሊሰጣቸዉ እንደሚችል ተደነንግጓል፡፡

ምዝገባን በተመለከተ የጥብቅና ፍቃድ እና የጥብቅና ድርጅቶችን ፍቃድ ሰርተፍኬት የማስጠት ሀላፊነት ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የተሰጠ ሀላፊነት በመሆኑ እነዚህን አካላት መዝግቦ መረጃቸዉን መያዝ ለማህበሩ ከማስጠት ይልቅ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማስጠቱ መረጃ አያያዙን ይበልጥ ወጥታማ እና ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ለመመደብ ቀላል ስለሚያደርገዉ በአንቀጽ 17(1) ላይ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ጠበቃ እና

የጥብቅና ድርጅቶችን ማዝገቦ እንዲይዝ ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ይሁንና እነዚህ የተማዝገቡ አካላት የጠበቆች ማህበር አባል የመሆን ግዴታ ስላለባቸዉ እና በማህበሩ በድጋሜ እንዲማዝገቡ ከማስገደደድ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የማዝገባቸዉን ስም ዝርዝር በየ3 ወሩ ለማህበሩ እንዲሳወቅ ሀላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንቀጽ 18 (1) እና (2) ላይ ማንኛዉም ጠበቃ የህግ ጉዳይ ጸሀፊ፣ የጠበቃ ረዳት ወይም ሌሎች ሰራተኞች መቅጠር እንደሚችል እንዲሁም የጥብቅና ድርጅት ጠበቃ ከሚቀጥራቸዉ ባለሞያዎች በተጨማሪ ፍቃድ ያላቸዉን ጠበቆች መቅጠር እንደሚችሉ ነገር ግን ሁለቱም አካላት የቀጠሯቸዉን ባለሞዎች በተቀጠሩ በሁለት ወራ ዉስጥ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማስማዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ በንኡስ ቁጥር 3 ላይ ደግሞ በህግ ጉዳይ ጸሀፊ ወይም በጠበቃ ረዳትነት መቀጠር የሚችሉት ተዘርዝረዋል፡፡

የፍቃድ እደሳትን በተማለከተ በስራ ላይ ባለዉ አዋጅ አንድ ጠበቃ በአመት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃድ ማሳደስ እንዳለበት ይህ ካልሆነ የዲስፐሊን ክስ የሚቀርብበት ቢሆንም በዚህ ረቂቅ አንቀጽ 19 ላይ ግን ጠበቃዉ ፍቃድ በወቅቱ የሚያሳድስበት የተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች ስለሚኖሩ እና በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በዲሲፐሊን ከመቅጣት በፊት ሌሎች አማራጮች ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ፍቃዱን ማሳደስ ካለበት አንድ አመት በኋላ ባለዉ አንድ ወር ግዜ ዉስጥ የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ እንዲያሳድስ፤ ይህም ካልሆነ እና ፍቃዱን ያላሳደሰዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካለ የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ እንዲያሳድስ አማራጭ ተቀምጧል፡፡ ይሁንና በእነዚህ ሁሉ አማራጮች ፍቃዱን ያላሳደሰ ጠበቃ በዲሲፐሊን ማጠየቁ ፍትሀዊነት ስለሚኖረዉ የዲሲፐሊን ክስ ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ፍቃድ ለማሳደስ መሟላት ያለባቸዉ ሁኔታዎች በአንቀጽ 20 ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን ከነዚህም መካከል የህግ ስልጠና መዉሰዱን የሚገልጽ ማስረጃ፣ የጠበቆች ማህበር አባልነት መዋጮ መክፈሉን የሚገልጽ ማስረጃ፤ እና እድሜያቸዉ ከ70 አመት በላይ የሆኑ ጠበቆች ደግሞ የጤና ሁኔታቸዉን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚሉ ማስፈርቶች የተካተቱ ናቸዉ፡፡ እድሜያቸዉ ከ 70 አት በላይ ላሉ ጠበቆች የጤና ምርመራ ማጠየቅ ያስፈለገበት ምክንያት በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በተደረገ ጥናት አንዳንድ በእድሜ የገፉ ጠበቆች በአብዛኛዉ በአግባቡ የማዳመጥ እና የማንበብ ክህሎታቸዉ ዝቅ ያለ ሆኖ በአግባቡ ጉዳዮችን ተረድተዉ ተገቢዉን የጥብቅና አገልግሎት ባለማስጠታቸዉ በባለጉዳዮቻቸዉ ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ በሚረጋገጡነዉ፡፡

በዚህ ክፍል በመጨረሻ ላይ የተቀማጠዉ የጥብቅና ፍቃድ የሚማለስባቸዉ ሁኔታዎችን የተማለከተ ሲሆን አሁን ባለዉ አሰራር ጠበቃዉ ፍቃዱን መማለስ ሲፈልግ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የጥብቅና ደብተሩን የሚረከበዉ ጠበቃዉ የግብር ክሊራንስ ይዞ ሲቀርብ ነበር ይህም አሰራር የጠበቃዉ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የግብር ክሊራንስ እስኪሰጠዉ ድረስ ሰፋ ያለ ግዜ ስለሚወስድ እና ደብተሩ በጠበቃዉ እጅ ስለሚቆይ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ደግሞ በነዚህ ግዜያት ጠበቃዉ በጥብቅና ደብተሩ ሲገለገል ነበር የሚል ግምት ስለሚወስድ ለጠበቃዉ አገልግሎት ማቆሙን የሚገልጽ ማስረጃ ለማስጠት አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ በማሆኑም ጠበቃዉ ፍቃዱን

ለመሟላስ ሲያማላክት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የፍቃድ ደብተሩን ወድያዉኑ ሚከብ እንዳለበት እና ጠበቃዉ የግብር ክሊራንስ ሲያቀርብ የጥብቅና አገልግሎቱን ሚቋረጡን የሚገልጽ ሚስረጃ እንደሚሰጠዉ ተማላክቷል፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 3 ላይ ጠበቃዉ የጥብቅና ፍቃዱን ሚልሶ ማግኘት ከፈለገ እና ፍቃዱን ከማለሰ ሁለት አመት ከሆነዉ ለደረጃዉ የሚሰጠዉን ፈተና እንደሚዉስድ የተቀማጠ ሲሆን ይህም የሆነበት ግለሰቡ ከጥብቅና አገልግሎት ለሁለት አመት ሰርቅ ማዎዉ የሚፈልገዉ ተገቢ እዉቀት ላይኖረዉ ስለሚችል ያማላከተበትን የጥብቅና ፍቃድ ደረጃን የሚምጥን እዉቀት ያለዉ ስለማሆኑ ሚፈተሽ ስለሚያስፈልገዉ ነዉ፡፡

## 2.3 ክፍል ሶስት

የዚህ ረቂቅ አዋጅ ክፍል ሦስት ጠበቆች ስላሉባቸው ወይም ስለሚጠበቅባቸው የሚያ ግዴታዎች የሚደነግግ ሲሆን ይህ ክፍል በአራት ንዐሳን ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ንዐስ ክፍል አንድ ስለጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ የሚደነግግ ሲሆን ንዐስ ክፍል ሁለት ተከታታይ የሕግ ስልጠና ስለመዉሰድ ይደነግጋል፡፡ ንዐስ ክፍል ሦስት ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ስለሚሰጡበት ሁኔታ ሲደነግግ፤ ንዐስ ክፍል አራት ደግሞ ጠበቆች መድን ስለሚገቡበት ሁኔታ እና ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች የደንበኛን ንብረት ስለሚይዙበት አግባብ ይደነግጋል፡፡

በንኡስ ክፍል አንድ የተካተተቱትን ስንማላከት አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የጥብቅና ፍቃድ ሳይኖራቸው ፍቃድ ያላቸው አስማስለው የጥብቅና አገልግሎት ለማስጠት ይሞክራሉ፡፡ በማሆኑም ይህንን ዓይት ሕገወጥ ድርጊት ለሚከላከል አንዱ መንገድ ማንኛወም ጠበቃ በሚማላከተው አካል ሲጠይቅ ፍቃዱን እንዲያሣይ ሚድረግ በማሆኑ አንቀጽ 22 /1/ በዚሁ አግባብ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ይህ ረቂቅ አዋጅ ከማዘጋጀቱ በፊት በተደረገው ጥናት አንዳንድ ጠበቆች የጥብቅና ፍቃዳቸወን ለሌሎች ሰዎች ማልገያ አሳልፈው እየሰጡ ማሆኑ ስለተረጋገጠ ማንኛወም ጠበቃ የጥብቅና ፍቃዱን ለሌላ ሰዉ ማልገያ አሳልፎ ማስጠት እንደሌለበት ተደንግጓል፡፡

ሌላው በዚህ ንዑስ ክፍል አፅዕኖት የተሰጠው ጉዳይ የአገልግሎት ዉል የሚፈፀምበት አግባብነው፡፡ የአገልግሎት ዉል ግልፅ ማሆን ጠበቃው ወይም የጥብቅናው ድርጅት እና ደንበኛው መብትና ግዴታቸወን በግልፅ እንዲያወቁት ያደርጋል፡፡ ዉሉ የአገልግሎቱን ወሰን /Scope/ እና የአገልግሎት ክፍያ ማጠንና የአከፋፈል ዘዴወን የሚገልፅ በማሆኑ ግንኙነታቸው ሥርዓት ባለው አካሄድ እንዲሄድ ይረዳል፤ ከአላስፈላጊ ክርክር ይታደጋቸዋል፡፡ ስሆነም ጥብቅና አገልግሎት ዉል በጽሁፍ ማሆን እንዳለበት በአንቀጽ 23(1) ላይ ተማላክቷል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ዓይነት የጥብቅና አገልግሎት ዉል በፅሁፍ እንዲደረግ ሚድረግ የአገልግሎት ሰጪወን ጊዜ የሚሻማ እና ለአፈፃፀምም የሚይመች በማሆኑ ለአጭር ጊዜ የሚሰጥ ምክርን

በተማከተ በቃል ማስማማት የሚቻል ለማሆኑ በልዩ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ንዑስ ክፍል ሌላኛዉ ትኩረት የቢሮ ጉዳይ ሲሆን አንዳንድ ጠበቆች ሥራቸዉን የሚሰሩበት ቢሮ የሌላቸው ለመሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ጠበቃ ደንበኛዉን ከቢሮ ዉጪ ለማነጋገር የሚቻል ቢሆንም ጠበቃው ሥራዉን በዋናነት ሊሰራ የሚገባው በቢሮ ዉስጥ ነው፡፡ ቢሮ ጠበቃው የሚገኝበትን አድራሻ የሚያመለክት ሲሆን አገልግሎቱም ክብሩን በጠበቀ ሁኔታ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ምክንያቶች ታሳቢ በማድረግ ማንኛዉም ጠበቃ ቢሮ ሊኖረው ይገባል የሚል ድንጋጌ በአዋጅ ዉስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ስለታማኝነትና የፍትህ አጋር ስለመሆን የሚደነግገው አንቀጽ 24 በመሠረቱ የሚገልፀው መርህ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የፍትህ ሥርዓቱ ዋነኛ አጋዥ ኃይል ነው የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ መነሻ መርሀችን ይህ ከሆነ ደግሞ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ጉዳዩ ማጓተት፣ ሀሰተኛ ማስረጃ ማዘጋጀትና ማቅረብ እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች ሊፈፀም የለበትም ይልቁንም ፍ/ቤት ሲቀርብ ጉዳዩን በሚገባ አጥንቶ መቅረብ፤ ተገቢዉን ክርክር ማቅረብ እና ሌሎች መሰል ተግባራትን ሊፈፀም አለበት፡፡ በመሆኑም አሉታዊ ድርጊቶችን ለመከላከል እና አዎንታዊ ድርጊቶችን ለማበረታታትና ባለሙያው የፍትህ ሥርዓቱ ዋነኛ አጋዥ ኃይልም መሆኑን ለማሳየት ድንጋጌው በዚህ አግባብ ተቀርጾዋል፡፡ ሌሎች ከጠበቃ ስነ-ምግባር ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን ደግሞ በአንቀጽ 24(3) በተደነገገዉ መሰረት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ቦርዱ ወይም ማህበሩ በሚያወጡት እና በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በኩል በሚፀድቅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደሚወሰን ተመልክቷል፡፡

በንኡስ ክፍል ሁለት ላይ በዚህ ረቂቅ አዋጅ እንደ አዲስ ከተካተቱ ዋና ዋና ሀሳቦች መካከል የጠበቆች ህግ ስልጠና የመዉሰድ ግዴታን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዉበታል፡፡ በፍጥነት በሚለዋወጥ አለም ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እራሱን በጊዜው ካለዉ እዉቀት ጋር እያበቃ የሚሄድ ካልሆነ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቃት ላይኖረዉ ይችላል፡፡ ባለሙያው ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና አዳዲስ የሕግ ፅንሰ ሃሳቦች ጋራ እራሱን የሚያስተዋዉቅበት የግል ጥረቱ እንዳለ ሆኖ በሕግ እና በሥርዓት የሚመራ ሥርዓት ማዘርጋት ወቅቱ የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በአገራችን በየጊዜው አዋጆች ደንቦች እና መመሪያዎች በፌደራል እና በክልል ደረጃ ስለሚወጡ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ አዳዲስ የሕግ ፅንሰ ሃሳቦች ስለሚፈልቁ፤ ልማዳዊ አሰራሮችም ስለሚዳበሩ አንድ ባለሙያ ሕግ ትምህርት ቤት በተማረው ትምህርት ብቻ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡ የሥራ ላይ ስልጠና በባህርይው በትምህርት ቤት ከሚሰጠው መደበኛ ትምህርት በእጅጉ ይለያል፡፡ በሥራ ላይ የሚሰጥ ሥልጠና በመሠረቱ በተግባር ደረጃ /በአፈፃፀም ከገጠሙ ችግሮች በመነሳት የሚዘጋጅ በመሆኑ ለሥልጠናው በሚለዩት ነጥቦች ጭምር ከመደበኛው ትምህርት በመሠረታዊነት ይለያል፡፡ በመሆኑም በንዑስ ክፍል ሁለት ጠበቆች በግዴታ ሊወስዷቸው ስለሚገቡ ተከታታይ ሥልጠናዎች ይደነግጋል፡፡ ይህ ንዑስ ክፍል ስለተከታታይ ስልጠና አላማ፣ ስልጠናው ስለሚሰጥበት ጊዜ ርዝመት፣ ስልጠናዉን ስለሚሰጡ ተቋማት፣ የኢትዮጵያ የፌደራል ጠበቆች ማህበር የተከታታይ ስልጠና ግዴታን

በማከፈፀም ረገድ ስላለበት ኃላፊነትና ተያያዥ ጉዳዮች ያወሳል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ እንደተማከተውም ተከታታይ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ ከዓማቃዊ የፍቃድ እድሣት ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

ንኡስ ክፍል ሶስት ደግሞ ስለ ነጻ የጥብቅና አገልግልት ግዴታ የሚዋትት ሲሆን ፍትህ ሥርዓቱ የተደራሽነቱ አንዱ መለጫ ሰዎች በገንዘብ እጦት ወይም በኢኮኖሚዊ ምክንያት ከፍትህ አደባባይ እንዳይርቁ ማድረግ ነው፡፡ ፍትህ ማገኘት ወይም መብቱን ማስከበር የሚቻለው የኢኮኖሚ አቅም ያለው ብቻ ሣይሆን አቅም የሌለውም ጭምር ነው የሚለው የፍትህ ተደራሽነት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ የፍትህ ተደራሽነት መለጫ አንደኛዉ ደግሞ ጠበቃ ለመቅም ለማይችሉ ሰዎች የጥብቅና አገልግሎት በነፃ የሚገኝበትን ሥርዓት ማመቻቸት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ንኡስ ክፍል የነፃ አገልግሎቱን የአገልግሎት ወሰን /Scope/ ለማከፋት ተሞክሯል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ላይ የፍትህ ሥርዓቱን ለማሻሻል በሚሰሩ ኮሚቴዎች ወስጥ በአባልነት በማገልገል እና ለተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶና የማህበረሰብ ተቋማት የሕግ አገልግሎት በማስጠት የነፃ አገልግሎት ግዴታን ለመወጣት የሚቻል ለማሆኑ ተደንግጓል፡፡

በንኡስ ክፍል አራት ላይ ጠበቃወና የጥብቅና ድርጅቱ መድን ስለሚገባበት ሁኔታና በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገቡትን የደንበኛወን ንብረት ስለሚያስተዳድርበት አግባብ ተወስቷል፡፡ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ በደንበኛው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ካሣ የሚሆን መድን ሊገባ እንደሚገባ የተደነገገ ሲሆን ሌሎች አገሮችም ተመሣሣይ ሕግ አላቸው፡፡ በአዋጁ ወስጥ ይህ ሃሳብ እንዲካተት የተደረገበት ዋነኛ ምክንያት የደንበኛወን የካሣ መሠረት ለማከፋት ነው፡፡ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ካሣወን መክፈል ባይችል መድን ሰጪው ካሣወን ይከፍላል ማለት ነው፡፡ ሌላኛዉ የጠበቆች ግዴታ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገቡትን ንብረቶች ከራሱ ለይቶ ንብረትለይቶች በአግባቡ የመያዝ ግዴታ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጋችን ላይ አንድ ወኪል የወካዩን ንብረት እንደሚልካም አባት ሊያስተዳድር ይገባል የሚለው መርህ በዚህ ንኡስ ክፍል ላይ በሚገባ ተንፀባርቋል፡፡ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ይህንን ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን እንዲከታተል ለፌዴራል ጠበቆች ማህበር በአንቀጽ 63 ላይ ሰፋ ያለ ሥልጣን እና ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 2.4. <u>ክፍል አራት</u>

በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ላይ በዝርዝር የተደነገገዉ ሀሳብ የጥብቅና ድርጅትን የተመለከተ ሲሆን የጥብቅና ድርጅት በመሠረታዊነት የሚያስፈልገው ደንበኛው ድርጅታዊ ዋስትና እና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ ለማስቻል ነው፡፡ ድርጅታዊ ዋስትና ባለው አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆን ደንበኛ የጠበቃው መታመም፣ መሞት፣ ከአገር መውጣት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ኃላፊነትን ለመወጣት አለመቻል አገልግሎቱን አያጓደልበትም፡፡ በጥብቅና ድርጅቶች ማገልገል የዳበረ የሕግ ሥርዓት ባላቸው አገሮች

ተሟሯጭ የአገልግሎት አሰጣጥ ማንገድ ይሄው ነው፡፡ በርካታ ጠበቆች በጥብቅና ድርጅት አማካይነት አገለግሎቱን ለማስጠት ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 199/1992 የተሟ የሕግ ስርዓት ባለማዘርጋቱ የጥብቅና ድርጅቶች ተፈጥረዉ የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት የሚችሉበትን ፍቃድ ማስጠት ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የጥብቅና ድርጅት ከምስረታው ጀምሮ ያለውን ሂደት በግልፅ መደንገጉ ለአገልግሎት ፍቃድ ስለሚጠየቡትና አገልግሎቱ ስለሚሟሩበት ሁኔታ ለማወቅ የሚረዳ በመሆኑ ክፍል አራት ስለ ጥብቅና ድርጅት በዝርዝር የሚደነግጉ አንቀጾችን ይዞ ራሱን ችሎ ተዋቅሯል፡፡

የጥብቅና ድርጅትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሲቀረፁ መሠረታዊና አከራካሪው ጉዳይ የነበረው ድርጅቱ ምን አይነት ቅርጽ ይኑረው የሚለው ነበር፡፡ በአርቃቂዎች እና በጥናት ቡድኑ መካከል ሰፊ ወይይት ከተደረገ በኋላ የተደረሰበት መደምደሚያ ከሌሎች አገሮች ልምዶችም አንፃር ድርጅቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር መልክ አደረጃጀት ቢኖረው ይሻላል የሚል ነው፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት የድርጅቱ ኃላፊነት ወደ ሽሪኮች የግል ሃብት እንዳይሄድ ለመካላከልና አደረጃጀቱን ሳቢና ተሟሯጭ ለማድረግ ነው፡፡ አስፈላጊነቱን በተመለከተ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንቶች በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ከውጭ ሀገር የሚመጡ ባለሃብቶች እና ሌሎች አለም አቀፍ ተቋማት ከግለሰብ ጠበቃ ይልቅ ከጥብቅና ድርጅት ጋር ደንበኝነት መመስረትን ስለሚመርጡ እና በሀገራችን ያሉ እና ኢንቨስት ሚድረግ የሚፈልጉ ትላልቅ የዉጭ ሀገር ባለሀብቶች በሀገሪቷ ወስጥ የጥብቅና ድርጅቶች መኖራቸዉን እንደ ቅድሚያ መስፈርት እየወሰዱ በመሆኑ የጥብቅና ድርጅትን የሚመለከት የሕግ ማዕቀፍ ማዘርጋትን አስፈላጊ እና ወቅታዊ ደርገዋል፡፡ የአዋጁ ክፍል አራት የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም ስለሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ድርጅቱ ስላለው መብት፣ ሽሪኮቹ ስላላቸው መብትና ግዴታ፣ ስለመዋጮ አይነት፣ ስለትርፍ እና ኪሣራ ክፍፍል፣ የድርጅቱ ስያሜ ስለሚሟጥበት ሁኔታ፣ ስለ ድርጅቱ አስተዳደር እና ድርጅቱ ስለሚፈርስበት ሁኔታ በዝርዝር ያወሳል፡፡ በዚህ ክፍል ያሉ አንዳንድ አንቀጾችን ለማብራራት ያክል በአንቀጽ 42 ላይ ክህሎት ዋነኛ መዋጮ ለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 51 ላይ የጥብቅና ድርጅቶች ወይም ሽሪኮቻቸዉ የግብር አከፋፈልን በተመለከተ የተለየ ድንጋጌ ማስቀመጥ አሁን በስራ ላይ ካለዉ የሽርክና ማህበርን የተመለከቱ የግብር ህጎች ጋር ሊጋጭ ስለሚችል እና ወደፊት የሚመለከተዉ አካል የጥብቅና ድርጅትን የግብር አከፋፈል በተመለከተ ከአለም አቀፍ ተሞክሮ አንጻር የግብር ህጉን እንዲያሻሽል ሲወሰን ሊሻሻል ስለሚችል አሁን ካለዉ የግብር ህግ ጋር ለማጣጣም ሲባል የጥብቅና ድርጅት ወይም ሽሪኮቻቸዉ የግብር አከፋፈል አግባብነት ባላቸዉ የሽርክና ማህበርን የተመለከቱ የግብር ህጎች እንዲወሰን ተደንግጓል፡፡

## 2.5. ክፍል አምስት

ሌላው በረቂቅ አዋጁ ክፍል አምስት ላይ ስለ ጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር የሚደነግግ ሲሆን ረቂቅ አዋጁን ከነባሩ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992

የሚኖየው ማዕረታዊ ጉዳይ የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስርዓትን በተመለከተ ነው፡፡ በማዕረቱ ማንግስት የጥበቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ስራዉ ወደፊት ሙሉ በሙሉ በጠበቆች ማህበር እንዲሠራ ፍላጎት ያለዉ ቢሆንም በአሁን ወቅት ይህን ትልቅ ሀላፊነት ሙሉ በሙሉ መዉጣት የሚችል ጠንካራ የጠበቆች ማህበር ባለመኖሩ ይህ ማህበር በዚህ ረቂቅ አዋጅ አቋቁሞ እዉን ማድረግ የዚህ አዋጅ አንዱ ዓላማ በመሆኑ ይህ እስኪሆን ድረስ በረቂቅ አዋጁ ክፍል ሁለት ላይ እንደተገለጸዉ የጥብቅና ፍቃድ የመስጠት ስልጣን በጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ተወስኖ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በኩል እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስራን በተመለከተ በሶስት ዋና ዋና ህጋዊ ሰዉነት ባላቸው ተቋማት ማለትም በጠበቆች ማህበር፣ በጠበቆች አስተዳደር ቦርድ እና በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በጋራ እንዲሠሩና የጋራ ቁጥጥር እንዲደረግበት ተደርጎ በክፍል አምስት ስር እንዲጠቃለል ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍል ስር ሶስቱ የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር አካላት በሶስት ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍለው የየራሳቸዉን ድርሻ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስርዓቱን ከላይ በተጠቀሱት ሶስት አካላት እንዲሠራ መደረጉ በአሁን ወቅት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እየሠራ ያለዉን የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስርዓት ሶስቱ አካላት ስራዎችን በመከፋፈል የጋራ አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት እንዲተገብሩ የሚያደርግ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሲነሳ የነበረዉን የገለልተኝነት ጥያቄ ለፈታ በሚችል መልኩ የአወቃቀር፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱ እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡

አንደኛዉ በንዑስ ክፍል አንድ (ከአንቀጽ 57-68) ስር የጠበቆች ማህበር ተቋቁሞ ስልጣንና ሃላፊነቶቹ የተደነገጉ ሲሆን ማህበሩ ሁሉንም የፌደራል ጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች በአባልነት እንዲያቅፍ ተደርጓል፡፡ እያንዳንዱ ጠበቃና የጥብቅና ድርጅት በጥብቅና አስተዳደር ስርዓቱ ማለፍ እንዲችል እና የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብም ተገቢና ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ለማስቻል ማንኛውም የፌደራል ጥብቅና ፍቃድ ያለው ጠበቃና የጥብቅና ድርጅት ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስገዳጅነት የጥብቅና ማህበሩ አባል እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ማህበሩ በዋናነት ከአባላቱ በሚሰበሰብ መዋጮ እራሱን ችሎ ሙሉ ሃላፊነቱን ለመወጣት በሚችልበት ደረጃ ላይ እስከሚደርስ ድረስ የሚያስፈልገዉን በጀት በተመለከተ በመንግስት ድጋፍ እንዲደረግለትና የማህበሩ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤም በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እንዲጠራ በሚያስችል ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ማህበሩ በዋናነት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ፕሬዝደንት፣ ምክትል ፕሬዝደንት እና ዋና ፀሀፊ አካላትን የያዘና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ሰራተኞች፣ የስራ ክፍሎችና ኮሚቴዎች እንዲኖሩት በሚያስችል መልኩ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ የማህበሩን ስልጣንና ተግባር በተመለከተም ማህበሩ በዋናነት ከተከታታይ የጠበቆች የህግ ስልጠና የመዉሰድ ግዴታ ጋር በተያያዘ፣ ከጠበቆች የአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር በተያያዘ፣ እንዲሁም የደንበኞችን መብት በማስከበርና ደንበኞች ተገቢዉን የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ማህበሩ የራሱን አሰራርና አደረጃጀት በወስጠደንብ መወሰን እንዲችል ከመደረጉም በላይ አጠቃላይ የማህበሩ ስልጣንና ተግባራት የማህበሩ ወሳኝ አካላት

ለሆኑት ማለትም ለጠቅላላ ጉባኤው፣ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው፣ ለፕሬዝዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዝደንቱና ለዋና ፀሀፊው በተዋረድ ተመንዝሮ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ሁለተኛው የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስርዓትን እንዲቆጣጠር የተቋቋመው አካል የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ሲሆን በክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሁለት (ከአንቀጽ 69-78) ስር ተቋቁሞ ይገኛል፡፡ የቦርዱን አወቃቀር በተመለከተ ቦርዱ ገለልተኛና እራሱን ችሎ በነፃነት ወሳኔ ማስጠት እንዲችል ከጠበቆች ማህበር በዛ ያሉ ተወካዮች በማያዝ፣ እንዲሁም ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት የሚወከሉና ሰባት አባላት እንዲኖሩት ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡ ቦርዱ በዋናነት ማህበሩ በሚሰጣቸው ወሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን፣ በዲሲፕሊን ጉባኤው በሚሰጡ ወሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን፣ በጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና በጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በሚሰጡ ወሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በይግባኝ ሚልክ የሚያይ፣የመመርመርና የመወሰን ስልጣን እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ቦርዱ እራሱን ችሎ እስከሚጠናከር ጽህፈት ቤቱ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማስሪያ ቤት ስር እንዲደደራጅለት፣ የቦርድ አባላት ክፍያ እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሀይል፣ ቁሳቁስ እና በጀትም ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እንዲሟላለት ተደርጎ የተቋቋመ ሲሆን ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የወስጥ አሰራር ስርዓት በመሜያ መወሰን እንዲችል ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡ የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ፤ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ገለልተኝነታቸው እንዲጠበቅና በነፃነት መወሰን እንዲችሉ ለማድረግ ለቦርዱ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ ነፃነቱንና ገለልተኝነቱን በሚያስጠብቅ ሚልኩ ከጠበቆች ማህበር፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚወጣጡ ሰባት አባላት እንዲኖሩት ተደርጎ የተቋቋመ ሲሆን ጉባኤው በዋናነት የጠበቆችና ጥብቅና ድርጅቶች የስራ አፈፃፀም የጥብቅና ስነምግባር ደንብን የተከተለ መሆኑን የሚከታተልና ይህን ለመተግበር የሚያስችል ስርዓት የማዘርጋት፣ የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ ደንብን እና ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች የሚቀርቡ የዲሲፕሊን ክሶችን የመመርመርና የመወሰን እንዲሁም ከጠበቆች ስነምግባር ጋር በተያያዘ ጥናት የማካሄድና የጥናት ወጤቱን ለጠበቆች አስተዳደር ቦርድ የማቅረብ ስልጣንና ሃላፊነት እንዲኖረው ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡

የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ሁለተኛው ለጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ተጠሪ የሆነ አካል ሲሆን በተቻለ ማጠን የኮሚቴወን ገለልተኝነት ሊያስጠብቅ በሚቹል ሁኔታ ከጠበቆች ማህበር፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት የሚወጣጡ ሰባት አባላት እንዲኖሩት ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴው በዋናነት የፌደራል ጥብቅና ሙያ ችሎታ መመዘኛ ፈተና የማዘጋጀት፣ የሚፈተን፣ ፈተናወን በአግባቡ የሚረም፣ የፈተና ወጤትን በአግባቡ የማሳወቅ፣ የማለፊያ ነጥብ የመቁረጥ እና ወጤትን በተገቢው ቦታ በግልጽ የማሳወቅ ተግባርና ሀላፊነት

የተጣለበት ሲሆን አጠቃላይ የፈተና ስነ-ስርዓት ደንብ በማዘጋጀት ለቦርዱ አቅርቦ የሚፀድቅና ሲጸድቅም ተግባራዊ የሚደረግ ስልጣንና ሀላፊነት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ከጠበቆች ማህበር፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ከፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወጣጡ አምስት አባላት የሚኖሩት የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ገለልተኛ ሆኖ ተዋቅሮ ለቦርዱ ተጠሪ እንዲሆን የተደረግ ሶስተኛ አካል ነው፡፡ የሆነ አካል ሲሆን እንዲያቋቁም ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ኮሚቴ የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ሰው ከማመልከቻው ጋር አያይዞ የሚቀርባቸው ማስረጃዎች የጥብቅና ፍቃድ ሊያሰጡ ስለመቻል አለመቻሉ በመመርመር የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ መወሰን እንደሚችል፤ ስለጥብቅና ፍቃድ ጠያቂው አካል ስነ-ምግባር ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ለማወቅ የሚያስችሉ ማስረጃዎችን በራሱ ተነሳሽነት ማስቀረብና መመርመር የሚያስችል ስልጣንና ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ሌላኛው የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር ስርዓትን የሚቆጣጠር አካል የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሲሆን የተቋሙ ስልጣንና ሀላፊነትም በረቂቅ አዋጁ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሶስት አንቀጽ 82 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በዋናነት የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በሚሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት የጥብቅና ፍቃድ የመስጠት፤ የጥብቅና ፍቃድ የማደስ፣ የጥብቅና ድርጅቶችን የመመዝገብ፣ ከጠበቃና ከጥብቅና ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞችን ተቀብሎ የመመዝገብ፣ የጥብቅና ፍቃድን የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ዉሳኔ በዲስፕሊን ኮሚቴ ሲወሰን የማገድ ወይም የማሰረዝ፣እና ሌሎች ስልጣንና ሃላፊነቶች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

## 2.6. ክፍል ስድት

ሌላኛው ወሳኝ የረቂቅ አዋጁ አካል ስለዲሲፕሊን ጥፋትና ቅጣት የሚደነግገው ክፍል ሲሆን በረቂቅ አዋጁ ክፍል ስድስት (ከአንቀጽ 83-95) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ክፍል የዲሲፕሊን ጥፋት አይነቶችን ቀላል እና ከባድ ብሎ በማለየትና ለቀላልና ከባድ ዲሲፕሊን ጥፋቶች ሊጣል የሚገባውን የዲሲፕሊን ቅጣት አይነት ወይም መጠን በግልጽ ለይቶ አስቀምጧል፡፡በተጨማሪም ስለይግባኝ፣የወንጀል ድንጋጌዎች፣ የማየም ሂደት እና ተፈፃሚነቱ ደንግጓል፡፡

የጥብቅና ፍቃድን ለደንበኛና ለሚያመለከተው አካል ካለማሳየት፣ የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥበት ጉዳይ የደረሰበትን ደረጃና ያለበትን ሁኔታ ለደምበኛ ካለማሳወቅ፣ የፍርድ ቤት ቀጠሮን አክብሮ ካለማገኘት፣ ያለበቂ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ ከመጠየቅ፣ ለጠበቆች ማህበር መከፈል የሚገባን መዋጮ በወቅቱ ካለመክፈል፣ የጥብቅና ፍቃድን በወቅቱ ካለማሳደስ እና ሌሎች መሰል ጥፋቶች በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ስር ተካተዋል፡፡ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ቅጣትን በተመለከተ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች በጥፋቶቹ ክብደት ላይ የሚመሰረት ሆኖ የቃል ማስጠንቀቂያ፣ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እና ከብር ሶስት ሽ እስከ ብር ሰባት ሽ በሚደርስ ገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጡ በየጥፋቶቹ አይነት ተለይተው ተደንግገዋል፡፡

ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች እና ቅጣቶች በተማለከተ በጠበቃ ረዳትናትና ህግ ጉዳይ ፀሃፊነት እንዳይቀጠሩ በአዋጁ የተከለከሉ ሰዎችን ከመቅጠር፣ የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በህጉ አግባብ በወቅቱ ካለማስመዝገብ፣ የተከታታይ የህግ ስልጠናን ካለመውሰድ፣ የደንበኛን ሚስጥር ካለማጠበቅ፣ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታን ካለወጣት፣ የጥብቅና ስራን በድለላ ከማስራት፣ የጥብቅና ወል ስምምነትን በጽሁፍ ካለማድረግ፣ የጥብቅና ወልን ያላግባብ ከማቋረጥ፣ የጥብቅና መድን ግዴታ ካለመግባት፣ የጥብቅና ፍቃድ ሳይመለስ በቋሚ ስራ ላይ ከማስሜራት፣ የጥቅም ግጭት ከሚያስነሱ ጉዳዮች፣ ከጥብቅና ፍቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት ከማስጠት፣ የደንበኛን ማስረጃ በአግባቡ ካለማቅረብ፣ የጥብቅና አገልግሎት ማስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት ማስጠት ጋር የተያያዙ ጥፋቶች፣ ከአቅም በታች ከመከራከር፣ የጥብቅና ፍቃድን አላግባብ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ከማስጠት፣ ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ከመማከጠር፣ ማስረጃ ከማጥፋት፣ የህግ ማስረት የሌለውን ጉዳይ ከመያዝ፣ ሐሰተኛ ማስረጃ ከማቅረብ ወይም ከማስቀረብ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች፣ እንዲሁም ከማጭበርበር፣ ስርቆት እና ማታለል ጋር በተያያዙ ከጠበቃ| ` ስነምግባር ጋር ተቃራኒ በሆኑ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ተብለው ተለይተዋል፡፡ የከባድ ዲሲፕሊን ጥፋቶች ቅጣትን በተማለከተም የቅጣት አይነቶቹና ማጠኑ በዋነኛነት በጥፋቶቹ ክብደት ላይ የሚመሰረት ሆኖ ከብር ሰባት ሽ አምስት መቶ እስከ ብር አስራ አምስት ሽ፣ ከብር ሃያ ሽ እስከ ብር ሰላሳ ሽ፣ እስከ 6 ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፍቃድ ማታገድ፣ እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፍቃድ ማታገድ እና የጥብቅና ፍቃድ ማሰረዝ የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃዎች የሚያስወስዱ የዲሲፕሊን ጥፋት አይነቶች ተለይተዋል፡፡ ከዲሲፕሊን ጥፋትና ቅጣት ጋር በተያያዘም አሁን በስራ ላይ ባለዉ ህግ ያልተካተቱ እና እንደ ክፍተት ሲነሱ የነበሩ የዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ይርጋ፣ ይግባኝ፣ የወንጀል ቅጣት እና ማስየም ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች በዚህ ረቂቅ በግልጽ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ ስነ-ስርዓትን በተማለከተ የዲሲፕሊን ጉዳይ በባህሪው ከወንጀል ጉዳይ የተለየ በመሆኑ በመደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ከሚመራ ይልቅ የራሱ ስነ-ስርዓት ቢኖረው የተሻለ ስለሚሆን የዲሲፕሊን ክስ ቀራረብ ስርዓት ቦርዱ በሚያወጣው ስርዓት ማስረት እንዲመራ ተደርጓል፡፡ የዲሲፕሊን ክስ የይርጋ ጊዜን አስሜልከቶም ለቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ጥፋቶቹ በተፈፀሙ በአንድ ዓመት ጊዜ ወስጥ፣ እንዲሁም ለከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ጥፋቶቹ በተፈፀሙ በሁለት ዓመት ጊዜ ወስጥ የዲሲፕሊን ክስ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድና ክስ ማቅረብ እንደሚይቻል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የወንጀል ቅጣትን በተማለከተም በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መቀጣት በወንጀል የሚያስጠይቁ ጉዳዮችን በተማለከተ ከተጠያቂነት የሚያስቀር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወንጀል ጥፋቶችም በሌሎች የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች የተደነገጉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወንጀል ድንጋጌዎችን ማዘርዘር ሳያስፈልግ ድርጊቱን የፈፀሙ ጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በሚያስችል አግባብ ተደንግጓል፡፡

የማስየም ሂደትን በተማለከተ በነባሩ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 ስር ያልተካተተ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን ይህ የማስየም ስርዓት ድንጋጌም በወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ት ያለወና የወንጀልም ሆነ የዲሲፒሊን ቅጣት አላማ የሚይቃረንና አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በዲሲፕሊን ተከሶ ጥፋተኛ የተባለ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የዲሲፕሊን ቅጣቱ ከተሰጠ ከሁለት ዓመት በኋላ የማስየም ማመልከቻ ለዲሲፕሊን ጉባኤው ማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ፣ የማስየም ስርዓት፣ የማስየም ወጤቶች፣ ተፈፃሚ ት እና ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በተማለከተ የማስየም ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ከሶስት ዓመት በኋላ በራሱ ጊዜ እንደተሰየመ መቆጠር የሚችልበት ሁኔታ በረቂቅ አዋጁ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## 2.7. <u>ክፍል ሰባት</u>

የረቂቅ አዋጁ የሚጨረሻ ክፍል ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን (ከአንቀጽ 96-101) የያዘ ሲሆን ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣንን በተማለከተ አዋጁን ለማስፈፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የማውጣት ስልጣን እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን አዋጁን እና ደንቡን በተገቢው ሁኔታ ለማስፈፀም እንዲቻል ለማድረግ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ እና የጠበቆች ማህበር በአዋጁ በግልጽ የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸውን የየራሳቸውን ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ስልጣን እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

የሽግግሪያ ድንጋጌን በተማለከተም የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ እና የጠበቆች ማህበር ከዚህ አዋጅ መጽደቅ በሀኋላ የሚቋቋሙ አዲስ አካላት በመሆናቸዉ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸዉን ስልጣን እና ተግባራት ወድያዉ ሚፈጸም ስለማይችሉ በአንቀጽ 98(1) መሰረት ሁለቱ አካላት አዋጁ ከወጣ በኋላ ባለዉ ሁለት አመት ወስጥ ተቋቁመዉ በአዋጁ የተሰጣቸዉን ተግባር እና ሀላፊነት እንዲረከቡ የግዜ ገደብ ተቀምጧል፡፡ እስከዚያዉ ድረስ ግን ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በነባር ህጎች አግባብ ከጥብቅና አገልግሎት ስራ ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚፈፀም ስልጣን እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

ሌላዉ የዚህ አዋጅም አላማም ሆነ የመንግስት ወሳኔ የጥብቅና አገልግሎት ሙያ በሂደት ራሱን በራሱ ማስተዳደር የሚችልበትን ሁኔታ እና አቅም መፍጠር በመሆኑ ምንም እንኳን አሁን አዲስ ለሚቋቋመዉ ማህበር የጥብቅና አስተዳደር ስራዉን ጠቅልሎ ማስጠት ሙያወም ደንበኞችም ሊጎዱ እንደሚችሉ በማሰብ ለቦርዱ እና ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የተሰጡ የተለያዩ ስልጣን እና ተግባራት በተለያዩ የግዜ ገደቦች ወደ ማህበሩ የሚተላለፉበት የሽግግሪያ ግዜ ገደብ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት በአንቀጽ 74(3) ለቦርዱ ተጠሪ የሆኑት የፈተና ኮሚቴ እና የዲስፕሊን ጉባኤ የሁለቱም ወይም የአንዱ ተጠሪነት ቦርዱ ማህበሩ ብቁ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት አመት ግዜ ዉስጥ ወደ ማህበሩ እንደሚተላለፍ ተቀምጧል፡፡ በተመሳሳይ

ሁኔታ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ደግሞ የጥበቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ተጠሪነትን በማንኛውም ግዜ ቦርዱ ለማህበሩ ሊያስተላልፍ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በአንቀጽ 82(1)-(2) እና (6) ላይ የተመለከቱተን ስልጣን እና ተግባራቱን ማህበሩ ሀላፊነቶቹን ለሚከብ ብቁ መሆኑን ባረጋገጠ በማንኛውም ግዜ ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀላፊነቶች ሊያስተላልፍ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ሆኖም እነዚህ ስልጣን እና ተግባራት ከተላለፉ በኋላ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተግበራቱ በአግባቡ ስለመፈጸማቸዉ የመከታተል እና ኦዲት የማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ የመዉሰድ ወይም የማስወሰድ ሀላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ረቂቅ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩና በመታየት ላይ ያሉ ከጥበቅና አገልግሎት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በነባር ህጎች ማስረት ፍጻሜ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የተሻሩ ህጎችን በተመለከተም ነባሩ የፌዴራል ጠበቆች አዋጅ ቁጥር 199/2000 ሙሉ በሙሉ በረቂቅ አዋጁ የተተካ ሆለሆነ እንዲሻር የተደረገ ሲሆን አጠቃላይ አዋጁን የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው ተደርጓል፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 199/2000 ማስረት የወጡ ደንብና መመሪያዎች አዲሱን አዋጅ እስካልተቃረኑና በአዲሱ አዋጅ ማስረት በሚወጡ አዲስ ደንብና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

## 3. <u>ማጠቃለያ</u>

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ይህ የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ የጥብቅና አገልግሎትን አንድ እርምጃ ወደፊት የሚወስድ እና ሀገሪቷ አሁን ያለችበትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለዉጦችን ታሳቢ ባደረገ እና አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በማንዘብ የተዘጋጀ ረቂቅ በመሆኑ በሀገሪቱ የፍትህ ዘርፍ ላይ አንድ እሴት የሚጨምር ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

https;//chilot.me